# ህሊና ቢስ

ህሊና የሌለው ፤ ለሆዱ ያደረ
ትርፍና ኪሳራ ፤ ብሎ እየ ቆጠረ
ትግልን በገንዘብ ፤ እየመነዘረ
በፖለቲካው ላይ ፤ እያመነዘረ
ሀገሩን ወገኑን ፤ እጅ እግር ያሰረ
ምነው ባይፈጠር ፤ ሽል ሆኖ በቀረ ።

ለኔ አልተስማማኝም ፤ ሆድ አደር በሞላ
በትርፍ ኪሳራ ፤ ትግል እያሰላ
አገሩን ወገኑን ፤ የሚሸጥ ደላላ
ከናቱ ገዳይ ጋር ፤ አብሮ የሚበላ
ባሰስ በገሰሱ ፤ ሆዱን የሚሞላ
ምደቡ ካውሬ ነው ፤ ከነጣቂ ተኩላ ።

ከስጦታ ሁሉ ፤ አምላክ ሲበድለው
ልቡን ፈሪ አድርጎ ፤ ምላስ ብቻ አደለው
ትልቁን ስጦታ ፤ ህሊና ነፈገው
አይምሮውን ሁሉ ፤ በገንዘብ መረገው
ምግባረ ብልሹ ፤ ከንቱ ሰው አረገው ።

ፍርድ የሚገመድል ፤ ሀሰተኛ ዳኛ
ላገር ለወገኑ ፤ የማይቆም ምንደኛ
ለህሊና ቢሱ ፤ ዘራፊ ቀማኛ
መች አደለውና ፤ ለመሆን ሀቀኛ ።

ልቦናው ያልዳኘው ፤ ተለማምጦ አዳሪ
ከህሊናው ይልቅ ፤ ባለ ስልጣን ፈሪ
ለሀገሩ ሳይሆን ፤ ለግሉ ነዋሪ
ወገኑን ሀገሩን ፤ ፍጥረት አሳፋሪ
አፍም ቢወሰልት ፤ ለእውነትን ተጠሪ
ከህሊና በላይ ፤ ማን አለ መካሪ ።

ታዛቢው